# የሜዳይ እና የኒሻን ህግ አስፈላጊነት በኢትዮጵያ

**ጥናቱን ያከናወኑ ባለሙያዎች:-**

ይድነቃቸው ከበደ

1.በመንግሥታዊ አካላት ውስጥ ያለው የመረጃ አደረጃጀት ሥርዓት በአመዛኙ መረጃ የማግኘት መብትን ተፈጻሚነት እውን ለማድረግ በሚያስችል ዘመናዊ መልክ የተዋቀረ እንዳልሆነ፤ የመረጃ አደረጃጀትና አጠባበቅ ተቋማዊነት እንደሚጎድለውና በግለሰቦች እውቀትና ተሞክሮ ላይ የሚወሰንባቸው ሁኔታ መኖሩን ጥናቱ አመልክቷል፡፡ ይህንን ችግር ለመቅረፍ የህዝብ ግንኙነት ቢሮዎችን በሰው ሃይል፣ በገንዘብና ቁሳዊ ግብአቶች አጠናክሮ ሥለመረጃ ነጻነት አዋጁ ያላቸውን ግንዛቤ በማጎልበት ቀልጣፋና ፈጣን የመረጃ ፍሰትን የሚያረጋግጥ ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል፤

2. የመረጃ ነጻነት አዋጁን ተፈጻሚነት ለማረጋገጥ የህብረተሰቡ ግንዛቤ መዳበር የላቀ ሚና እንደሚጫወት እሙን ነው፡፡ ጥናቱ እንዳመለከተው የመብቱን ተፈጻሚነት እውን ለማድረግ በሚያስችል ደረጃ ሕብረተሰቡ እንዲሁም የመንግሥታዊ አካላት ሠራተኞችና ሃላፊዎች በቂ ግንዛቤ አላቸው ለማለት አይቻልም፡፡ በመሆኑም ሰፊ የግንዛቤ ማዳበር ስራዎች በመስራት የዜጎችን ንቃተ ህሊና ማሳደግና መረጃ የመጠየቅ ባህልን ማዳበር ያስፈልጋል፡፡ ለዚሁ ዓላማ እንደ ሬድዮና ቴሌቪዝን ያሉ የመገናኛ ብዙሃንን፣ የከተማ ማሥታወቂያ ሰሌዳዎችን፣ በራሪ ወረቀቶችን የመሳሰሉትን ዘዴዎች መጠቀም ያስፈልጋል፤

3. በመንግሥታዊ አካላት አሰራር ውስጥ የሚንጸባረቀው የሚስጥረኝነት ባህል መረጃ በማግኘት መብት ላይ የተጋረጠ ዋነኛ ተግዳሮት እንደሆነ ጥናቱ አመልክቷል፡፡ ይህንን አፍራሽ ባህልና የአሰራር ዘይቤ ለመለወጥ የመንግሥታዊ ተቋማት አሰራር እንዲሁም የተቋማቱ ሠራተኞችና ሃላፊዎች አስተሳሰብና የሥራ ባሕል መረጃ ማግኘት የዜጎች ሕጋዊ መብት፤ መረጃ መስጠት ደግሞ የተቋማቱ ሕጋዊ ግዴታ መሆኑን የተገነዘበና በዚሁ እሳቤ የሚመራ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንጻር የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ለሕዝብ ግንኙነት ባለሙያዎች የሰጠውን ስልጠና አድማስ በማስፋት ለሌሎች የመንግስት ሰራተኞችና ሃላፊዎች የሚዳረስበትን ሁኔታ ቢያመቻች የተቀላጠፈ የመረጃ ፍሰት ሥርዓት እውን ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

4. ለመረጃ አገልግሎት የሚከፈል ክፍያን አስመልክቶ ወጥ የሆነ ዝርዝር ደንብ አለመኖሩ በተቋማት የፋይናንስ

አቅም ላይ ሊያሳድር ከሚችለው ተፅዕኖ በተጨማሪ ወጥነት ያለው የክፍያ ሥርዓት አለመኖር በመረጃ አሰጣጥ ሥርዓቱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ስለሚያሳድር በተቻለ ፍጥነት ደንቡ እንዲያወጣ ማድረግ ያስፈልጋል።

5. አዋጁ ያስቀመጣቸው የመረጃ ክልከላ ምክንያቶች (በተለይም መከላከያና የሃገር ደህንነት ጉዳዮች) ምክንያታዊ ያልሆኑ ጭፍን የመረጃ ክልከላ ውሳኔዎችን ለማሳለፍ ሽፋን ሊሆኑ የሚችሉበት ሰፊ አጋጣሚ በመኖሩ የክልከላ ምክንያቶቹን ለአፈጻጸም በሚያመች መልኩ የሚያብራራ ዝርዝር ደንብ ወይም መመሪያ ቢወጣላቸው ያልተገባ የመረጃ ክልከላን መጠን ለማጥበብ ያስችላል።

6. “መገናኛ ብዙሃን አጋላጭ የሆኑትን ጨምሮ መረጃዎችን የመሰብሰብና የማሰራጨት መብት ያላቸው መሆኑ” እንዲሁም “የመንግሥት ሃላፊዎች ለግለሰቦችና ለመገናኛ ብዙሃን መረጃዎችን የማቅረብ” ሕጋዊ ግዴታ ያለባቸው መሆኑ በመረጃ ነጻነት አዋጁ የተረጋገጠ ቢሆንም በዚህ ሕጋዊ አግባብ መረጃ ለማግኘት የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት ከፍተኛ ችግር እንዳለባቸው ጥናቱ አመልክቷል። የመረጃ ጠያቂውን ተቋም በተናጠል ዒላማ ያደረጉ ግልጽና ምክንያት አልባ የመረጃ ክልከላዎችን ጨምሮ በተራዘመ ቀጠሮ አሰላችቶ ወይም በዝምታ ጥያቄውን አለመመለስ በስፋት የሚታይ ችግር መሆኑ የመገናኛ ብዙሃኑ መረጃን በእውቂያና መልካም ግንኙነትን በመሰሉ ኢ-መደበኛ (informal) ዘዴዎች የማግኘትን አማራጭ እንዲከተሉ አስገድዷቸዋል። የመንግስት ተቋማት ከመገናኛ ብዙሃን ከሚቀርቡላቸው “አጋላጭ” የመረጃ ጥያቄዎች ይልቅ በህብረተሰቡ የሚቀርቡ አገልግሎት ነክ የመረጃ ጥያቄዎችን በተሻለ ሁኔታ እንደሚያስተናግዱ ጥናቱ አመልክቷል። መረጃ የማግኘት መብት ተግባራዊነት ከሚያስገኛቸው ጠቀሜታዎች አንዱ ሕዝብ በመንግሥት አስተዳደር ላይ ቁጥጥር እንዲያደርግ ማስቻሉ ነው። ይህ የላቀ ጠቀሜታ ያለው ዓላማ ግቡን ይመታ ዘንድ መንግሥታዊ አካላት ሕጋዊ ግዴታቸውን ተገንዝበው መልካም ገጽታዎቻቸውንና ስኬቶቻቸውን የሚገልጹ መረጃዎችን ለመስጠት ካላቸው ፈቃደኝነትና ቅልጥፍና ባልተናነሰ መልኩ ከመገናኛ ብዙሃን የሚቀርቡላቸውን ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ይዘት ያላቸው የመረጃ ጥያቄዎች

የሚያስተናግዱበትን የአሰራር ሥርዓት እውን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡